# በሲያታል ከተማ የዜና እና የግንኙነት ቴክኖሎጂ ለነዋሪዎች ከፍትነትና ተቀባይነት ሪፖርት፤

## የሲያትል ከተማ ነዋሪዎች በኢንተርኔት የመገናኛ ዘዴዎች የመንግስትን አገልግሎት ለማግኘት ምን ያህል ተገናኝተዋል?

የሲያትል ነዋሪዎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መገናኛዎች፣በኮምፒውተር፣ በኢንተርኔት፣ በሽቦ-አልባ ስልክ፣ በፌስ-ቡክ፣ በትዊተር ምን ያህል እንደሚጠቀሙ ለመረዳት ጥናት ያደርጋል። ይህንኑ በሚመለከት፤ ነዋሪዎች በኮምፒውተር ለመጠቀም መስመር ላይ ሲገቡና አስፈላጊ አገልግሎት ለማግኘት ሲሞከሩ የሚገጥማቸውን ችግር አስተውለን፤ ነዋሪዎች መረጃ እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉና ለመንግሥትም ሆነ ለኮሚኒቲ ማሕበሮች አስተያየታቸውንም እንዴት መስጠት እንደሚሹ ማወቅ እንፈልጋለን። ከበታች የሚከተሉት አብይ ግኝቶች ባደረግነው ጥናት ከየኮሚኒቲው ባገኘናቸው ግንዛቤዎች መሠረት፤አብረው ያሳላፍናቸው አስተያየቶችና መደምደሚያ ሃሳቦች ይገኛሉ። በ 2013 ዓም ከ 2600 በስልክ ጠይቀን እንደተረዳነውና በተለያዩ ስድስት ቋንቋዎች ባካሄድነው ዘጠኝ የተለያዩ ኮሚኒቲዎች አትኩሮ ማስተዋል፣ በሌሎች ጥናቶች ጊዜ በአግባብ ላልተወከሉ ነዋሪዎች መልካም ምሳሌ ናሙናዎች ሆነው አግኝተናቸዋል። ከዚህ በታች ያሉት አስተያየቶች ውጤቶችም፣ በሲያትል የሰፊው የመገናኛ ቴክኖሎጂ አገልግሎት ክፍትነትና የሰውም ተቀባይነት የተባለው ሰፊ ሪፖርት አንዱ ክፍል ነው። *ቀጣዩ እርምጃ ወደትክክለኛው የእኩልነት ዲጂታል እድል፤*የሲያተል ከተማ አስተዳደር ከነዋሪዎቹ የቀረበውን አስተያየት በወግ ማጤን፤ ለየኮሚኒቲው ማድረግ የሚገባውን ውሳኔዎችን፣ የድረ-ገጽ እቅዱን እንደምን መቀየስ እንዳለበት፣ በዚህ ወቅት የሚታየውን የተዛባ የዲጂታል አደላደል አሰተካክሎ በሚገባ ለማጥበብ እንዲያስችለው፣ ከመገናኛ የሽቦ መስመር ባለቤቶች ኩባንያዎች ከሌሎችም ጋር በሕብረት ለመስራት ይጠቅመዋል። ከ 2000 ዓም ጀምሮ ከተማው ይህን መሰል ጥናት ሲያጠናቅር ይህ አራተኛው ጊዜ ነው። ጥናቱም የተካሄደው በሲያትል ከተማ አስተዳደር በመገናኛ ቴክኖሎጂ ክፍል፤ የኮሚኒቲ ቴክኖሎጂ ፕሮግራም ውስጥ ነው።

### ዓብይ ግኝቶች፤

- በሲያትል የኢንተርኔት አገልግሎት እያደገ በመሄዱ፣በየቤቱ ተጠቃሚው ቁጥሩ እያደገ ሄዷል፣በጥናታችን ከተሳተፉት 85% በትኩረት ቡድን ሆነው ካስተዋልናቸው ደግሞ 75% በአንድ መልክ ሆነ በሌላ ከቤታቸው በኢንተርኔት መስመር መግባት የሚችሉ ናቸው።

- ሲያታል፣ የተጓዥ (ተንቀሳቃሽ) ኢንተርኔት ኮሚኒቲ ነው። ስለሆነም፣72%የላፕቶፕ ባለቤት፣ 66% የብልጥ ሽቦ-አልባ ስልክና (ታብሌት) የእጅ ኮምፒውተር ተጠቃሚ በመሆኑ፤ 55% የቤት ወይም የቢሮ ኮምፒውተር ግልጋሎትን አልፎታል። ከሲያትል ነዋሪ 89% የሚሆነው አዘውትሮ ሽቦ-አልባ ስልክ ተጠቃሚ ሲሆን፣ ከዚሁም ድግሞ 58% የብልጥ ሽቦ-አልባ ስልክ ባለቤት ነው። በአጠቃላይም ሲስተዋል በትኩረት ያስተዋልነው ቡድን በኢንተርኔት አጠቃቀሙ ላይ አነስተኛ ሆኖ፣ የሽቦ-አልባ ስልክ አጠቃቀሙ ግን ከሌላው ጋር ተመሳሳይ ነው።

- ጥናቱ እንደሚያመለክተው፣የማሕበራዊነት ተሳትፎ ለሲያትል ነዋሪዎች ዋጋ ያለው ቁም ነገር መሆኑ እንደቀጠለ ነው። በስልክ መጠይቅ ባካሄድነው ጥናት እንደመለሱልን፣ ከገሚሱ በላይ፣(53%) የሚሆኑትና በኢንተርኔት ጥናቱን ከተሳተፉት ደግሞ (77%) በኮሚኒቲ ማሕበራዊ ኑሮ ጉዳይ ውስጥ ይሳተፋሉ።

- በጥናታችን ተሳታፊዎች አባባል፡ ለኮሚኒትም ሆነ ለከተማው አስተዳደር አስተያየታችውን ለመግለጽ፣ ኢንተርኔት ተመራጭ መሆኑን ገልጸዋል። በስልክ መጠይቅ ከመለሱልን ደግሞ 75% የሚሆኑት፣ በኢንተርኔት ከተሳተፉት መሃል 87% ያህሉ፣ እና በትኩረት ካስተዋልናቸው ቡድኖች መሃል 38% የሚሆኑት በኢንተርኔት መስመር መጠቀምን ይመርጣሉ። የኮሚኒቲ ስብሰባዎችን በኢንተርኔት መሳተፉ ከፍተኛ ተመራጭነት አለው። ጥናታችንን በስልክ ከመለሱልን መሃል 58% እና በኢንተርኔት መስመር የጥናቱ ተሳታፊ ከሆኑት መሃል 71% ያህሉ በኢንተርኔት መስመር መሳተፍን ይመርጣሉ። በትኩረት ያስተዋልናቸው ቡድን ምርጫቸው የተለያየ ሆኖ፣ ለኮሚኒቲ ጉዳይ 38% በኢንተርኔት መሳተፍ 36% ደግሞ ለኮሚኒቲ ለስብሰባ መሳተፍ ሲመርጡ፣ 31% የሚሆኑ ግን በስልክ መጠየቁን ይፈቅዳሉ።

- መረጃዎችና ዜና ማስታወቂያዎችን ከከተማው እንዴት ማግኘት እንደሚፈልጉ ሲገልጹ፣ ሕብር ዘዴዎችን እንደሚመርጡ ይታያል። ምርጫቸውም በኢ-ሜል ወይም ለአጣዳፊ ጉዳይ (ቴክስት) በስልክ ጽሑፍ መልክት፣ ቢያገኙ ይመርጣሉ። በስልክና በኢንተርኔት በጥናቱ ከተሳተፉት መሃል 85% የሚሆኑት በስልክ፣ በኢ-ሜል ወይም በከተማው ዋና ድረ-ገጽ ላይ ቢወጣ፣ አለያም ፌስ-ቡክና በሌላ ዜና ማሰራጫዎች ቢደርሳቸው ሲፈቅዱ፣ በትኩረት ካስተዋልናቸው ደግሞ 60% ያህሉ በተመሳሳይ ዘዴ ቢደርሳችው ይመርጣሉ።

- አመርቂ የሆነ ተሳትፎ እንዲኖር፣ የተስተካከለ የማስተዋወቅ ዘዴና ከነውን በኢንተርኔት መስመርና ከዚያም በተለየ መንገድ ማካሄድን ይጠይቃል። የሲያትል ከተማ ነዋሪዎች ፌስ-ቡክን እና ትዊተርን በጣምራ ይጥቀማሉ። ይሁን እንጂ፣በአጠቃላይ ሁሉም ነዋሪ በዚሁ ዘዴ ተጠቃሚ ነው ብሎ ለመደምደም ያዳግታል። ከነዋሪዎቹ ስድሳ-ስድስት ከመቶ የሚሆኑት በፌስ-ቡክና 33% ደግሞ በትዊተር ተጥቀመዋል፤ ይሁን እንጂ፣ ከአብዛኛው ይልቅ ጥቂቱ አዘውትረው ይጠቀሙበታል።

- አቅማቸው ውስን ለሆኑት ነዋሪዎች፣ የኮሚኒቲ ቴክኖሎጂ መግቢያ ስፍራዎች እንዲኖራላቸው አስፈላጊ ነው። ጥናታችንን በስልክ ከመለሱልን አንድ-አምስተኛቸው፤በኢንተርኔት ከተሳተፉት ደግሞ፣45% ያህሉ በቤተ-መጽሓፍት ባሉት ኪምፒውተር ሲጠቀሙ፣15% ደግሞ በየኮሚኒቲው ማእከል በሚገኘው ኮምፒውተር ተጠቃሚ ናቸው። በየኮሚኒቲው ማእከል የኮምፒውተር መስመር ማግኛ ሥፍራ መኖሩ በጣም አስፈላጊ መሆኑ በሁሉም በትኩረት ባስተዋልናቸው ቡድኖች በደንብ ተረጋግጧል።

- አሁንም ቢሆን፣ የዲጂታልን ቴክኖሎጂ ለሁሉም በእኩሌታ የማዳረሱ ትኩረት፣ የኢንተርኔት አጠቃቀሙ ስልት ላይ እንጂ፣ መደበኛ መጠቀሚያ ሥፍራ ማቅረቡ ላይ ባይሆንም፣በኢንተርኔት ለመጠቀም መግቢያ ሥፍራ ማግኘቱና የአጠቃቀም ችሎታው ብቃት ጋር ገና ሰፊ ክፍተት ይታያል።

- ቴክኖሎጂን በወግ ተቀብሎ መጠቀሙ ላይ የትምሕርት ደረጃና እድሜ ወሳኝ መስለው ቢታዩም፤ በጥናቱ መሰረት፣ የገቢ መጠን እና የብሔር ልዩነት ጭምር መኖሩ ጎልቶ ይታያል። በትኩረት ካስተዋልናቸው ቡድኖች እንደተረዳነው፣ቋንቋ እና መሰራታዊ የባሕል ልዩነቶችም ይህንኑ ያመለክታሉ።

- በ 2009 ዓም በቀደሞ ጥናት ላይ በግልጽ ይታይ እንደነበረው፣ቴክኖሎጂን መቀበሉም ሆነ አግኝቶ መጠቀሙ በጾታዎች ላይ የነበረው ልዩነት፣ አሁንም እንደበፊቱ ጎልቶ የሚታይ ጉዳይ አይደለም።

- የብሮድ ባንድ እና የኬብል ቴለቪዥን ዋጋ ጉዳይ አሳሳቢ ቢሆንም፣የብሮድ ባንድ ማስተላለፍ ፍጥነት ሃይሉ ማደጉ ጠቃሚ እንደሆነ በጥናቱ የተሳተፉት እንደገለጹት፣በዚሁ ዘዴ ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት ሃያል መሆኑን ተረድተናል።

- ባለፉት አራት ዓመታት በኢንተርኔት ቪዲዮ የመመልከቱ አማራጭ እጅግ እያደገ በመሄዱ ምክንያት፣ የኬብል ቴሌቪዥን ደንበኞች ቁጥር 13% ቀንሷል።

- የሲያትል.ገቭ ድረ-ገጽ ለኮሚኒቲ አገልግሎት ጠቃሚ ቋት በመሆኑ፣ ብዙሃኑ በወግ ይጠቀሙበታል። በስልክ ጥናታችን ከተሳተፉት ሁለት-ሶስተኛው፣ በኢንተርኔት ከመለሱልን ደግሞ 85%፣ እና በትኩረት ካሰተዋልናቸው ቡድኖች ገሚሱ፣ ባለፈው ዓመት የሲያትልን ከተማ ዋና ድረ-ገጽ ጎብኝተዋል።

- ‹የሲያትል ቻነል› የተሰኘው (ቴሌቪዥን)ብዙ ተመልካች አለው። በቴሌፎን ጥናት ከመለሱልን 51% እና በኢንተርኔት ከመለሱት ደግሞ 66% ‹ሲያትል ቻነል›ን እንደሚመለከቱ አውቀናል። የቆዳ ቀለማቸው ነጭ ካልሆኑት መሃል ሁለት-ሶስተኛው ሳያሰልሱ በየሳምንቱ  የሲያትል ቻነል ተመልካች እንደሆኑ በስልክ ባደረግነው ጥናት ለማወቅ በቅተናል።

  ስለዚህ ጥናት ጠቅላላ ግኝት ሰፋ ያለ ማብራሪያ በሰፊው የቴክኒክ ሪፖርት ውስጥ ተተንትኖ ይገኛል።

**የሰጠነው አስትያየት (ሓሳብ)**

ለዚህ ሪፖርት የዜና እና የግንኙነት ቴክኖሎጂ መገኛኛ ክፍል ባደረገው ጥናት መሰረት፣ ከተማው ለኮሚኒቲው ምን ዓይነት እርምጃ፣ሊወስድ እንደሚችል፣የሚከተሉትን መደምደሚያ ሃሳቦች ያቀርባል፤

- በመላው ሲያትል ያለው የኢንተርኔት ፍጥነት እንዲጨምርና መስመር መግቢያ ሥፍራዎች እንዲበዙ ጥረቱን መቀጠል፤

- የገቢያቸው መጠን ዝቅተኛ ለሆኑ ነዋሪዎች፣በአቅማቸው መጠን የሚችሉት የኢንተርኔት አገልግሎትና መሳሪያ አማራጮች ማቅረቡ እንዲቀጥል ማበረታት። የሚቀርቡትም መጠቀሚያ ቁሳቁሶች ለተጠቃሚው ቀላል የሆኑና የማያስቸግሩ ለብዙ ቋንቋዎች የሚያገለግሉ መሆኖናቸውን ማረጋገጥ።

- ለአዛውንቶችና  የትምህርት ደረጃቸው አነስተኛ ለሆኑት የሚበጅ መሳሪያና አገልግሎት ከነአጠቃቀም እውቀቱ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በይበልጥ ማረጋገጥ።

- ስለኢንተርኔት መስመር አጠቃቀም ደንበኛ ግንዛቤ እንዲኖር ሥልጠናው እንዲቀጥል ማድረግ፤ ቤተ-መጻሕፍትና የኮሚኒቲ ማእከሎች፣በየኮሚኒቲው ያሉት የኮምፒውተር መለመማጃዎቸ እና የሲያትል የመንግሥት ትምሕርት ቤቶች በዚህ ጥረት ላይ ዋና ተባባሪዎች ይሆናሉ።

- የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው አነስትኛ ለሆነው ኮሚኒቲዎች ሁሉ እንቀስቃሴውን የማዳረሱን ጥረት በይበልጥ ማጠንከር።

- **ኢ- አግልግሎት- የአዘገጃጀትና አከፋፈል ስልት፤**

- በሚታተሙ፣በኢንተርኔት፣አለያም በማሕበራዊ ዜና ማሰራጫ፣በሞቢል ቪዲዮም ሆነ በሌላ ዜና ማዳረሻ ዘዴዎች ሁሉ በመጠቀም የከተማውን ዜናዎች ማሰራጨቱን መቀጠል።

- የዜና ማዳራሱ ነገር እንዲሰፋ፣ከኮሚኒቲ ቡድኖች ጋር ሕብረት መፍጠርና መተባበሩን ማጠናከር።

- የኢንተርኔትን ጥቅም አስመልክቶ፣የመገልገያ መሳሪያው ዋጋና፣የተቀጠበ አገልግሎት ፐላን ምን ያህል በእኩሌታ የሕዝብ መገልገያነቱን አዛብቶ እንዴት የጠቀሜታ ልዩነት እንደሚፈጥር መገመት። ምንም እንኳን የኤሌክትሮኒክ መጠቀም ችሎታቸው ዝቅተኛ የሆኑትም ሰዎች ቁጥር አናሳ ቢሆንም፣ዜና እንዲደርሳቸው ሰለሚፈልጉ ለእነዚሁ ሰዎች በሌላ ዘዴ ማድረሱን ማረጋገጥ።

- ብልጥ ስልክ (ስማርት-ፎን) ለሌላቸው ደግሞ፤የቴክስት መልክት እንዲደርሳቸው አገልግሎትን ማስፋፋት።

- አዲስ የኢንተርኔት አገልግሎት ለገበያ ሲቀርብና ሲዳብር፣የብዙ ብሔር ነዋሪዎች ስልጠና አግኝተው፣ ከአግልግሎቱ እንዲሳተፉ አድል መስጠቱን ማረጋገጥ። አዲስ ፐላን ሲቀየስና ሰኬታምነቱ ሲሞከር፣ የተለያዩ ብሔሮች ደንበኞች እንዲኖሩበት ማድረግ።

- አሁን ያለውና አዲስ የኮምፒውተር ፐሮግራም ሲነደፍ፣የየሰዉ የግል ሰነድ እንዴት ተጠብቆ እንደሚያዝና በሚስጥር ሌላ እንዳያገኘው እንክብካቤ እንደሚደረግለት ያለውን ጥበቃ ለነዋሪዎች ማስረዳት።

- በሕዝብ የኮምፒውተር መለማመጃ ማእከሎች መጥተው ሰለ ግላዊ ጤናቸው ጉዳይ ሆነ ስለሕግ ጉዳይ ለሚጠቀሙት ሁሉ ተጨማሪ በሥርአት አያያዝና ጠንካራ አጠባበቅ ትምሕርት መስጠት።

**የኬብል አገልግሎት**

- የኬብል መዳረሱ ዝቀተኛ በሆነበት አካባቢ፣የገበያ ማስፋፋቱ ጉዳይ ላይ በማተኮር፣የኬብል ኩባንያው የደንበኞች ቁጥር ማሳደጊያ ቢሮውን ተጠቅሞ ነዋሪውን ማስተማርና ደንበኛ እንዲሆን ማድረግ። ይህን መሰል ዜናዎች ሁሉ በተለያዩ ቋንቋዎች እንዲዘጋጁና በየማሕበራዊ ድርጅቶች የእንግሊዝኛ ችሎታቸው እጅግም ለሆነው ሁሉ ማዳረስ።

- የደንበኞች ቁጥር መቀነሱ ያስከተለው ለውጥ ምን እንደሆን ለመረዳት መሞከር ።

- **ማሕበራዊ ሚዲያና የሕዝብ ተሳትፎ፤**

- የከተማውን በሕዝባዊ ሚዲያ እንቀስቃሴ በተለይም በፌስ-ቡክ በይበልጥ መቀጠል።

- በሚገኘው መገናኛ ዘዴ ሁሉ ማለትም በስልክ፣በኢሜል ሆነ ቴክስት፣ከነዋሪዎች ጋር ለመገናኘት ሙከራውን መቀጠል። ለጊዜው ግን፣ከሰዎች ጋር ለግንኙነት ኢሜልን እንድዋና መገናኛ አድርጎ

መቀጠል። አጣዳፊ ማስታወቂያዎች/ማሳሰቢያዎች ሲኖሩ፣በቴክሰት፣በስልክ፣በኢ-ሜል ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክ ዘዴ መጠቀሙ፣ወዳጅ ከወዳጆች/ጎረቤቶች ጋር ዜናውን እንዲጋሩት ያበረታታል።

- የተለያዩ መገልገያ ዘዴዎች ማፍራቱን በመቀጠል አዳዲስ የኤሌክትሮኒክ መሳተፊያ ቅያሶችን ከግለ-ሰብ የተሳትፎ እድል ጋር በጣምራ አዋህዶ መንደፍ።

- ታላቅ ባንድ-ስፋት ካላቸው ኮሚኒቲዎች መልክቱን በቪዲዮ አድርጎ ከአንስተኛ ባንድ-ሰፋት ካለባቸው ስፍራዎች ደግሞ በኢንተርኔት መስመር የኮሚኒቲ ሰበሳባዎችን ብዙሃኑ እንዲሳተፉ አድርጎ የኮሚኒቲ ሰብሰባ ማካሄዱን በይበልጥ መቀጠል።

- ከየኮሚኒቲ ድርጅቶች/ማሕበሮች ጋር ያለውን ሕብረት በማጠንከር፣እነዚህ ማእከሎች የሕዝቡን ሰሜት ልመቃኝት/ሆነ የሲያትል.ገቭን/እና ሲያትል ቻነልን ለሕዝብ ለማሳወቅ አማካይ ሥፍራ በመሆናቸው ያለውን ሕብረት በደንብ መንከባከብ።

- የተለያዩ የቋንቋዎች ገጾች እይታ እንዲያገኙ፤ጥረት ማድርግና የተርጓሚዎችን ሥራ አጉልቶ ማሳየት።

- የተጻፉትን ሰንዶችና በእትመት የተያዙትን ሁሉ፣ ከስብሰባም ጊዜ ሆነ ወይም በፊት አለያም በኋላ በኤለክትሮኒክ ሰንድ መልክ መኖራቸውን አሰቀደሞ ማረጋገጥ። የማየት ችሎታቸው ደካማ ለሆኑት ሁሉ ማጉያ መነጽር ወይም ማንበቢያ ሰሌዳ አቅርቦ መርዳት።

በጠቅላላው ከሌሎች የትኩረት ቡድኖች ያገኘነውን ውጤት እና ሙሉውን ሪፖርት በ seattle.gov/tech/indicators ይመልከቱ።
ይህ ቀንብር የተዘጋጀው በሲያትል ከተማ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ክፍል በኮሚኒቲ ቴክኖሎጂ ክፍል ውስጥ ነው።
እኛን ለማግኘት communitytechnology @Seattle.gov ወይምfacebook.com/Seattle.com/SeattleCommunity/Tech ካልሆነ ደግሞ በስልክ ቁጥር (206)233-7877 ሊያገኙን ይችለሉ።